# ምዕራፍ 13



# ሕፃናትን ከወሲባዊ ጥቃት መከላከል

“መስማት የተሳናቸውን ሕፃናት መርዳት” በሚል መፅሐፍ ውስጥ ስለ ወሲባዊ ጥቃት የሚመለከት መረጃዎችን ማግኘት ምናልባትም እንግዳ ነገር ሊመስል ይችላል፡፡ የሚያሳዝነው ጉዳይ ግን መስማት የተሳናቸው ሕፃናት መስማት ከሚችሉት ሕፃናት ይበልጥ ለወሲባዊ ጥቃት የተጋለጡ መሆናቸው ነው፡፡ ስለዚህ የመስማት የተሳናቸው ሕፃናት ወላጆችም ሆኑ ለእነሱ የሚያስቡ ሰዎች ወይም መስማት የተሳናቸውን የሚያስተምሩ መምህራን ሁሉ ስለዚሁ ጉዳይ ቢያውቁት መልካም ነው፡፡

**ሕፃናትንን በጥንቃቄ እንጠብቅ**

ማንም ሰው ሕፃናትን ለወሲብ ቢጠቀም ወይም ቢሞክር በጥብቅ መወገዝ አለበት፡፡



- የቤተሰብ አባል (ሕፃን ወይም ጎልማሳ)
- የቤተሰብ ጓደኛ
- ጐረቤት
- አስተማሪ
- ሞግዚት

ማንኛውም ሰው ቢሆን ጥቃቱን መፈፀም አይችልም!




ሆኖም ግን ስለ ወሲባዊ ጥቃት ማውራቱ ከባድ ነው፡፡ በብዙ አካባቢዎች፡—

- ሰዎች ስለ ወሲባዊ ጥቃት (እንዴት እንደሚፈፀም፣ እና ስለሚያስከትለው ጉዳት) አያውቁም
- ሰዎች ስለ ወሲባዊ ግንነኙነት ለማውራት ይከብዳቸዋል
- ሰዎች በሕፃናት ላይ ወሲባዊ ጥቃት ይፈፀማል ብለው ስለማምኑ፣ ስለ ጉዳዩ ማሰብ ወይም ማውራት አይፈልጉም
- ለሕፃናት ስለወሲብ ማን መናገር እንደሚችል፣ ምን እንደሚነገር፣ እና ይህ ዓይነቱ ውይይት ምን ጊዜ መካሄድ እንዳለበት የማህበረሰቡ ባህላዊ ህጐችና ልምዶች ይወስኑታል፡፡

*በማንኛውም ሕፃን ላይ ወሲባዊ ጥቃት መፈፀም የለበትም!*
*እያንዳንዱ ጎልማሳ የሆነ ሰው ሕፃናትን ከጥቃት የመጠበቅ ኃላፊነት አለበት!*

## በሕፃናት ላይ ስለሚፈፀሙ ወሲባዊ ጥቃቶች አንዳንድ ተጨባጭ ነገሮች

የሕፃናት ወሲባዊ ጥቃት ማለት አንድን ሕፃን ለወሲባዊ ድርጊት መጠቀም ማለት ነው፡፡ ይህ ድርጊት በማንኛውም ሕፃን ላይ ሊፈፀም ይችላል፡፡ በሁሉም ማህበረሰቦች፣ በሀብታምም ሆነ በድሃ ቤተሰቦች ላይ ሊፈፀም ይችላል፡፡ ወሲባዊ ጥቃት በሴቶችም በወንዶችም ላይ ይፈፀማል፡፡ ወሲባዊ ጥቃት አብዛኛውን ጊዜ የሚፈፀመው ዕድሜአቸው ከ5 ዓመት በላይ በሆኑት ሕፃናት ላይ ሲሆን ከዚህ ዕድሜ በታች በሆኑትም ላይ የሚደርስበት ጊዜያት ጥቂት አይደለም፡፡

ወሲባዊ ጥቃት ምን ያህል በስፋት እንዳለ በትክክል አናውቀውም፤ ምክንያቱም ብዙዎቹ ሕፃናት የተፈፀመባቸውን ድርጊት አይናገሩም፡፡ ነገር ግን በዓለም ላይ ካሉት ሕፃናት ውስጥ ከአራቱ በአንዱ ላይ ወሲባዊ ጥቃት ሊያጋጥም ይችላል፡፡

### አንድን ህፃን በመንካት ጥቃት መፈፀም

- የግብረ ሥጋ ግንኙነት በአንድ ህፃን ላይ መፈፀም
- የአንድን ሕፃን ሀፍረተ ሥጋ ክፍሎችን መንካት ወይም አንድን ሕፃን የአንድ አዋቂ ሰውን ወይም የትልቅ ልጅን ሃፍረተ ሥጋ ማስነካት
- አንድን ህፃን አስገድዶ ሴተኛ አዳሪ እንድትሆን በማድረግ ገቢ ማግኘት

### አንድን ሕፃን ሳይነኩ ጥቃት መፈፀም

- ወሲባዊ ንግግርን ወይም ስዕሎችን በመጠቀም አንድን ሕፃን ማስደንገጥ፣ ለወሲብ እንድትነሳሳ ማድረግ፣ ወይም ስለወሲብ እንድታውቅ ማድረግ
- ሌሎች ሰዎች ወሲብ ሲፈፅሙ አንድን ሕፃን እንድታይ ወይም እንድትሰማ ማድረግ
- አንድን ሕፃን ለወሲባዊ አገልግሎት ፎቶ ማንሳት (ፖርኖግራፊ)
- አንድን ሕፃን ወሲባዊ የሆኑ ፎቶዎችን እንድትመለከት ማድረግ



አብዛኞቹ ወሲባዊ ጥቃትን ፈፃሚዎች ወንዶች ናቸው፡፡ እንደዚሁም በአብዛኞቹ የጥቃቱ ሰለባ በሆኑት ሕፃናት ላይ ጥቃቱን ያደረሱባቸው የሚያውቋቸው ሰዎች ለምሳሌ ዘመድ፣ የቤተሰብ ጓደኛ፣ ወይም ጎረቤት የሆኑ ሰዎች ናቸው፡፡ ጥቃቱ እንግዳ በሆነ ሰው እምብዛም አይፈፀምም፡፡ ጥቃቱ አንዳንድ ጊዜ ለረጅም ጊዜ እንዲያውም ለዓመታት ሊቀጥል ይችላል፡፡

በሕፃናት ላይ ወሲባዊ ጥቃትን የሚፈፅሙ ሁሉም ሰዎች አካላዊ ኃይል አይጠቀሙም፡፡ አንዳንድ ጊዜ በማግባባት ሕፃኗ ወሲብ ለመፈፀም ዝግጁ እንድትሆን ተፅዕኖ ያደርጉባታል፡፡ በማሳመንና ‘ደግ’ በመሆን፣ በማስፈራራት፣ ወይም ስጦታዎችን በመስጠትና ማስፈራሪያዎችን በማድረግ ጥቃቱን ሊፈፅሙ ይችላሉ፡፡ (ጥቃት የሚፈፅመው የሕፃኗ ጓደኛ የሚመስለው መስማት የተሳነው ሰውም ሊሆን ይችላል፡፡) አንድ ሰው ወሲባዊ ጥቃቱን ለመፈፀም የሚጠቀመው ኃይል፣ ማስፈራሪያ፣ ወይም ‘ደግ’ በመምሰል ቢሆንም *የጥቃቱ ውጤት በአንድ ሕፃን ላይ በጣም ከፍተኛ ጉዳትን ያደርሳል፡፡*

## መስማት የተሳናቸው ሕፃናት ለወሲባዊ ጥቃት ለምን የተጋለጡ ይሆናሉ?

ሁሉም ሕፃናት ለወሲባዊ ጥቃት በሆነ ደረጃ የተጋለጡ ናቸው፣ ምክንያቱም የሚንከባከቧቸውን ጎልማሶችንና ታላቆቻቸውን ስለሚያምኑ ነው። ሕፃናት የተማሩት ‘ጥሩ ልጅ’ ማለት የተነገረውን የሚፈፅም ልጅ እንደሆነ አድርገው ነው። በዚህ ምክንያት ለጎልማሶች ‘እምቢ’ ለማለት ይከብዳቸዋል። ጎልማሳ ሰዎች ምን ዓይነት ባህሪ እንዳላቸው ወይም ትክክለኛ የሆነው የጎልማሳ ሰው ባህሪ ምን ዓይነት እንደሆነ ጨቅላ ሕፃናት በፍፁም አያውቁትም።

በተለይ መስማት የተሳናቸው ሕፃናት ለወሲባዊ ጥቃት የተጋለጡ ናቸው፤ ምክንያቱም፡–

- ማህበረሰቡ በአጠቃላይ የአካል ጉዳት የደረሰባቸውን ሰዎች ከሌሎች ሰዎች የበታች እንደሆኑ አድርጐ ይመለከታቸዋል። ከዚህም የተነሳ ጥቃት ፈፃሚው አንድን መስማት የተሳናትን ሕፃን ለወሲብ መጠቀሙ ምንም ማለት እንዳልሆነ አድርጐ ሊያስብ ይችላል። እንደዚሁም ሴት ልጆች ከወንዶች የበታች እንደሆኑ ተደርገው ስለሚገመቱ፣ በተለይም ደግሞ መስማት የተሳናቸው ልጃገረዶች መስማት ከተሳናቸው ወንድ ልጆች የበለጠ የበታች እንደሆኑ ተደርገው ይታሰባሉ። በመሆኑም መስማት የተሳናቸው ልጃገረዶች ከማንም በላይ ለአደጋው የተጋለጡ ናቸው።
- መስማት የተሳናቸው ሰዎች የአንድን ሰው ትኩረት በሚፈልጉበት ጊዜ፣ ‘መንካትን’ ለመግባቢያ ይጠቀሙበታል። በዚህም ምክንያት አንድ ሰው መስማት የተሳናቸውን ሕፃናት ሲነካቸው ወሲባዊ ዓይነት ቢሆንም እንኳ ችግር እንደሌለበት ሊቆጥሩት ይችላሉ።
- መስማት የተሳናቸው ሕፃናት ያላቸው መረጃ መስማት ከሚችሉት ሕፃናት ያነሰ ሊሆን ይችላል፤ ቢሆንም ግን ለማወቅ ያላቸው ፍላጎት ከፍተኛ ነው። በተጨማሪም የመገለል ወይም የብቸኝነት ስሜት የሚሰማቸውም ሊሆኑ ይችላሉ፣ ይህ ደግሞ ለጥቃት ፈፃሚዎች የተጋለጡ እንዲሆኑ ያደርጋቸዋል።
- ውስን የሆነ የመግባቢያ ክህሎት ያላቸው መስማት የተሳናቸው ሕፃናት፣ ሰዎች ለራሳቸው የሚፈልጉትን ነገር እንዲያደርጉላቸው በትዕዛዝ መልክ ሲጠይቁአቸው፣ ሕፃናቱ ለምን ብለው ሳይጠይቁ ማድረግን ብቻ ተለማምደው ሊሆን ይችላል።




- መስማት የተሳናቸው ሕፃናት የመግባቢያ ክህሎቶቻቸው ውስንና ያልዳበሩ በመሆናቸው፣ ስለ ራሳቸው ጥንቃቄ እንዲያደርጉ የሚነገራቸውን ሙሉ በሙሉ ላይረዱት ይችሉ ይሆናል።
- መስማት የተሳናቸው ሕፃናት ስለሚደርስባቸው ጥቃት ለማንም እንዳይናገሩ ውስን የሆነው የመግባቢያ ክህሎታቸው ትልቅ እንቅፋትም ይሆንባቸዋል። አንድ ሰው ሕፃኗ ስለሚደርስባት ጉዳይ ለማንም መናገር አትችልም ብሎ ስለሚያስብ፣ ጥቃቱን ሊፈፅም ይችላል። መስማት የተሳናቸው ሕፃናት የሚግባቡት ከቤተሰባቸው አባላት ጋር ብቻ ወይም ከሌሎች ከሚንከባከቧቸው ሰዎች ጋር ብቻ ሊሆን ይችላል። ጥቃቱን ፈፃሚው ደግሞ የቤተሰብ አባል፣ ሞግዚቷ፣ ወይም አስተማሪዋ ከሆነ ማንንም ስለማታምን ለማንም መናገር አትፈልግም ይሆናል።

## ወሲባዊ ጥቃት የማይጠፉ ጉዳትን ያመጣል

ወሲባዊ ጥቃቱ በተፈፀመበት ጊዜ አንድን ሕፃን ሊጐዳ ከመቻሉም በላይ ጉዳቱ በሕፃኗ የህይወት ዘመን ይቀጥላል:: ይህ ደግሞ በተለይ እውነትነት ያለው ተጠቂዋ ሕፃን ስለ ጥቃቱ መነጋገር ካልቻች ወይም ርዳታ፣ ድጋፍና ህክምና ማግኘት ካልቻች ነው::

## የማይጠፉ የአካል ጉዳት

የማይጠፉ የአካል ጉዳት በግብረ ሥጋ ግንኙነት በሚተላለፉ በሽታዎች ሊመጣ ይችላል:: ጥቃት ፈፃሚው ወደ አንድ ሕፃን ኤች አይ ቪ/ኤድስንና የጉበት በሽታን (hepatitis) ሊያስተላልፍ ይችላል:: እነዚህ በሽታዎች ደግሞ ሊድኑ የማይችሉ ናቸው:: ሌሎች የአባላዘር በሽታዎችም ካልታከሟቸው ለወደፊቱ ከእርግዝና፣ ከካንሰርና ከሌሎች ከባድ በሽታዎች ጋር በተያያዘ ሁኔታ ሞትን ሊያስከትሉ ይችላሉ:: ጥቃቱን ከፈፀሙባቸው ሰዎች ላይ የአባላዘር በሽታ የሚይዛቸው ሕፃናት ብዙውን ጊዜ የበሽታው ምልክቶች ወዲያው ስለማይታዩባቸው ህክምናም አያገኙም::



## በአንድ ሕፃን ዕድገት ላይ የሚደርስ ጉዳት

በወሲብ ጥቃት የደረሰባቸው ሕፃናት ከደረሰባቸው አካላዊ ጉዳት በተጨማሪም የጥፋተኝነት ስሜት፣ ሀፍረትና ንዴት በከፍተኛ ደረጃ ይሰማቸዋል:: ብዙዎቹ የወሲብ ጥቃት የደረሰባቸው ሕፃናት ሌሎች ሰዎችን ማመን አይችሉም:: በተጨማሪም የጥቃቱ ሰለባ የሆኑት በራሳቸው መተማመን የማይችሉ፣ ዋጋ-ቢሶችና ክብር የሌላቸው እንደሆኑ አድርገው ራሳቸውን ይቆጥራሉ::

## የጥቃት ዑደቶች

ወሲባዊ ጥቃት የደረሰባቸው ሕፃናት ህይወታቸውን በሙሉ በሌሎች ሲጠቁ ሊኖሩ ይችላሉ:: በሕፃንነታቸው በደረሰባቸው ጥቃት ምክንያት የፍቅርን ስሜት ወይም ከለላን ለማግኘት መንገዱ ወሲብ ብቻ እንደሆነ አድርገው በማመን ያድጋሉ:: በመጥፎ ሁኔታ መያዛቸውና በወሲብ በመጠቃታቸው ምክንያት በህይወታቸው እንደ መጥፎ አርአያ ሆነው ራሳቸውም ወደፊት ተመሳሳይ ድርጊት እንዲፈፅሙ ሊያደርጋቸው ይችላል::




ከጥቃቱ ለመፈወስ ድጋፍና እርዳታ ካልተገኘ፣ የተጠቁ ወንዶች በሚያድጉበት ጊዜ ራሳቸውም ጥቃት ፈፃሚ ይሆናሉ:: የዚህ ዓይነቱ የጥቃት ዑደት ለወደፊቱ ትውልድም ሌላ የጥቃቱ ሰለባዎች የሚሆኑንና ጥቃት አድራሾችን ይፈጥራል::

በሕፃናት ላይ የሚፈፀም የወሲብ ጥቃት ጉዳቱ ለሕፃናቱ ወይም ለቤተሰቦቻቸው ብቻ ሳይሆን ለመላው ማህበረሰብ የሚተርፍ ነው:: ለምሳሌ፣ በወሲብ ጥቃቱ ምክንያት እንዲሸማቀቁ የተደረጉ ወይም የተገለሉ ሰዎች አንዳንድ ጊዜ አጥፊዎች ወይም ጠበኞች ወይም ጠጪዎችና የአደገኛ ሱስ ተጠቂዎች እንዲሆኑ ሊያደርጋቸው ይችላል::

## ወሲባዊ ጥቃትን መከላከል




ሌሎች ሰዎች እኛን የሚይዙበት መንገድ ለራሳችን የምንሰጠውን ዋጋ ሊወስነው ይችላል። ሕፃናት ጥቅም እንደሌላቸውና ተስፋ እንደሌላቸው ተደርገው ሲነገራቸው፣ እነሱም ራሳቸውን የሚያዩት በዚሁ በተነገራቸው መንገድ ነው። ስለዚህ ሕፃናት ስለራሳቸው ጥሩ ስሜት እንዲኖራቸው ልናስተምራቸው ያስፈልጋል፤ ከዚያም በራሳቸው የሚተማመኑና በተሻለ ሁኔታ ራሳቸውን መከላከል የሚችሉ ይሆናሉ።

ሕፃናት ራሳቸውን እንዲጠብቁ ለማድረግ፣ ወሲባዊ ጥቃቶችን መከላከል እንዲችሉ (ከትላልቅ፣ ጠንካራና በጣም ኃይለኛ ከሆኑ ሰዎችም ጭምር) ዕውቀት፣ ክህሎቶችንና መተማመንን ልንሰጣቸው ይገባል።

## ስለ ወሲባዊ ጥቃት ልጅዎ መረዳትና መወያየት እንድትችል ይርዷት

መስማት የተሳናቸው ሕፃናት የበለጠ በቀላሉ መማር የሚችሉት ነገሮችን ማየት ሲችሉ ነው። ምልክቶችን፣ የሰውነት እንቅስቃሴዎችን፣ የፊት አገላለጾችን፣ ስዕላዊ ካርዶችን፣ አሻንጉሊቶችን እና ሞዴል ጨዋታዎችን በማሳየት አንድን መስማት የተሳናትን ሕፃን ከወሲባዊ ጥቃት ራሷን መጠበቅ እንድትችል ሊያስተምሯት ይችላሉ። የሚከተሉትንም እንድትገነዘብ ይርዷት፡–

- አንዳንዶቹ የመነካካት ዓይነቶች ፈፅሞ አይፈቀዱም። ለምሳሌ በእጅ መጨባበጥና ማቀፍ ሊፈቀድ ይችላል፣ ግን ሃፍረተ ስጋን መንካትና የመሳሳሉት እፀያፊ ንክኪዎች እንደማይፈቀዱ ይንገሯት
- አንድ የማትፈልገው ነገር በእሷ ላይ ከደረሰባት ልትነግርዎ እንደሚያስፈልግ
- በወሲባዊ መንገድ አንድ ሰው ሊነካት ከሞከረ እምቢ ማለት እንዳለባት አፅንኦት ሰጥተው ሊያስተምሯት ይገባል።

ለጨቅላ ሕፃናት (በተለይም ሕፃናቱ መስማት የተሳናቸው ከሆኑ) አንዳንድ ሃሳቦችን ለምሳሌ የግል፣ ሚስጢር፣ ማመን፣ መጠንቀቅና የመሳሰሉትን ቃላት በምልክት መግለፅ ከባድ ነው። በመሆኑም እነዚህን ሃሳቦች በተደጋጋሚ በመግለፅ እንዲገባት ማድረግ እንዳለብዎ አይዘንጉ።




ልጅዎ መረዳቷን እስከሚያረጋግጡ ድረስ የተለያዩ ምልክቶችን፣ አካላዊ እንቅስቃሴዎችን (gestures)፣ ስዕሎችን፣ እና ቃላትን ይጠቀሙ። ሁኔታዎችን በድርጊት ለማሳየት ይሞክሩ፣ ወይም አሻንጉሊቶችን ወይም ስዕሎችን በመጠቀም በተለያዩ ዘዴዎች እነዚህን ሃሳቦች ለማሳየት ይሞክሩ።

## ስለ ወሲባዊ ጥቃት ለመግለፅ የሚረዱ አንዳንድ የምልክት ምሳሌዎች




## ሕፃናት ስለ ጥቃቶች እንዲገልፁ ይርዱአቸው

የሰዎችን የምልክት ስሞች ሕፃናትም ይወቁት። ስለ ሰዎችና ስለ ቦታዎች በጥልቀት ለማስታወስ እየሞከሩ ከልጅዎ ጋር ይነጋገሩባቸው። ልጅዎ አንዳንድ ቃላትን እንደ ረጅም፣ አጭር፣ ፀጉራማ፣ ወፍራም፣ ቀጭን፣ እና ሌሎችንም መግለጽ እንድትችል ያስተምሯት። አንድ ሕፃን አንድን ሰው መግለፅ ከቻለች ጥቃት ፈፃሚውንም መግለፅ ትችላለች።

### ለእያንዳንዱ ሰው የምልክት ስም ይስጡት



ከትንንሾቹ ልጆቻችን ውስጥ፣ አንዷ የ6 ዓመት ዕድሜ ያላት መስማት የተሳናት ልጃችን ተደፍራ ነበር። ይህንን ድርጊት ማን እንደፈፀመባት ለማወቅ ፖሊስ እንድንጠይቃት ጠይቆን ነበር። ነገር ግን መልስ መስጠት አልቻለችም ነበር። ምክንያቱም በዙሪያዋ ላሉት ሰዎች ለሁሉም የምልክት ስም የላትም ነበር። አሁን ወላጆችን ለሚቀርቧቸው ሰዎች ሁሉ የምልክት ስም እንዲሰጧቸው እንገፋፋቸዋለን። በዚህ መንገድ ሕፃኗን ሊጐዳ የሚችል ማንም ሰው ቢሆን ስለሚታወቅ ወደ ህግ ማቅረብ ይቻላል።

—Nzeve Deaf Childern's Center, Zimbabwe, Africa

## ተግባራት

ልጅዎን ከወሲባዊ ጥቃት ለመጠበቅ የሚከተሉት ተግባራት ሊረዱ ይችላሉ

### ▶ አንዳንድ የሰውነት ክፍሎች የግል እንደሆኑ ልጅዎ መገንዘብ እንድትችል የሚረዱ መንገዶች




ለልጅዎ ሰውነቷ የራሷ ብቻ እንደሆነ ይግለፁላት:: በተጨማሪም ከሰውነት ክፍሎቿ በተለይ አንዳንዶቹ ከሌሎች የበለጠ የራሷ የግሏ እንደሆነ ያሳውቋት:: ትላልቅ ልጆችና ጎልማሶች ሀፍረተ ስጋዋንና የግሏ የሆነውን የሰውነት ክፍሏን መንካት እንደሌለባቸው እንደዚሁም እሷም የአዋቂ ሰዎችን የግላቸው የሆነውን የሰውነት ክፍላቸውን ቢጠይቋትም እንኳ መንካት እንደሌለባት ይግለፁላት:: አሻንጉሊቶችን ወይም ስዕሎችን በመጠቀም መንካት የሚፈቀድና የማይፈቀድ የሰውነት ክፍሎችን በልዩ ልዩ ዘዴዎች፣ ለምሳሌ በሰውነት እንቅስቃሴና በፊትዎ ላይ አገላለጾችን እየተጠቀሙ ያሳዩአት::

እንደዚሁም ደግሞ አንድ ሰው የግሉ የሆነን ነገር ወይም የግል የሆኑ ስዕሎችን ልጅዎ እንድትመለከት ቢጠይቃት የማይፈቀድ መሆኑን ይግለፁላት::

ልጅዎ ዕድሜዋ በ3 እና በ5 ዓመት መካከል በሚሆንበት ጊዜ፣ ስለ ሀፍረት ስጋዎችና ሌላ የግል ስለሆኑ የሰውነት ክፍሎች፣ እንዲሁም ስለ የወንዶችና የሴቶች ሰውነት ልዩነቶች ያስተምሯት::

እነዚህን ሀሳቦች ለማስተማር ከባድ ነው፣ ስለዚህ ልጅዎ መረዳቷን እርግጠኛ ለመሆን የተለያዩ ዘዴዎችን ለመጠቀም ይሞክሩ:: ማስተማሩ በተፈጥሮ መከናወን ይችላል፣ ለምሳሌ ልጅዎ ልብሷን በምትለብስበት ጊዜ ሊሆን ይችላል:: የሰውነት ክፍሎችን ለማስተማር አሻንጉሊትንም መጠቀም ይችላሉ::

### ▶ ልጅዎ እርዳታ በምትጠይቅበት ጊዜ እንዴት መጮህ ወይም ምን ዓይነት ድምፅ ማሰማት እንዳለባት እንድታውቅ መርዳት




ብዙ መስማት የተሳናቸው ሕፃናት ድምፃቸውን መጠቀም አይፈልጉም:: ምክንያቱም በሚናገሩበት ጊዜ ሰዎች ስለሚስቁባቸው ወይም ሲናገሩ ድምፃቸው እንደሚያስቅ ስለሚነግሩአቸው ነው:: አንድ ሰው በሚያስቸግረው ጊዜና እርዳታ ሲፈልግ መጮህ እንደሚፈቀድ ለልጅዎ ይግለፁለት::

‘እምቢ!፣ እምቢ!’ ወይም ‘እርዱኝ!’ በማለት መጮህ እንደሚችል ልጅዎን ያስተምሩት:: ወይም አንድ አዋቂ ሰው ወይም ትልቅ ልጅ ሊጎዳው ከሞከረ እግሩን መርገጥ፣ መጮህ፣ መንከስ ወይም መታገል ይችላል:: ለልጅዎ ሊነግሩት የፈለጉትን ለማሳየት አሻንጉሊት ሊጠቀሙ ወይም አስመስለው መጫወት ይችላሉ::

## ▶ ልጅዎ እምቢ ማለትን እንድትር እንዴት መርዳት ይችላሉ፡፡

መስማት የተሳናቸው ሕፃናት አንዳንድ ነገሮችን ለምን ማድረግ እንዳለባቸው ወይም የሆነ ነገርን ማድረግ እንዳለባቸው፣ ወይም ስለሚደርሱባቸው ነገሮች አብዛኛውን ጊዜ አይረዱም፡፡ ሰዎችን ለማስደሰት ስለሚፈልጉ ብቻ ያለ ምንም ጥያቄ ይታዘዛሉ፡፡ ይህ ሁኔታ ግን አንድ ሰው ስህተት የሆነ ነገር እንዲያደርጉ በሚጠይቃቸው ጊዜ ችግር ሊሆን ይችላል፡፡

ልጅዎ 'እምቢ' ማለትን እንድትለማመድ ይርዷት፡፡ በመጀመሪያ ህፃኗ 'እምቢ' ልትልበት የሚያስችላትን ሁኔታዎች ያመቻቹ፡፡




በኋላም፣ 'እምቢ' ስለማለትና ልጅዎ እርዳታ ከየት ማግኘት እንደምትችል ይነጋሯት፡፡




አንድ ሰው ልጅዎ የማይፈልገውን ነገር እንዲያደርግ ሲጠይቀው ሕፃኑ ለዕርሰዎ ወይም ለሌላ ጎልማሳ ሰው ወዲያውኑ እንዲነግር ይጠይቁት፡፡



## ▶ ልጅዎ አዋቂ ሰዎችን ሁልጊዜ መታዘዝ እንደሌለባት መገንዘብ እንድትችል እንዴት መርዳት ይቻላል

አንዲት ሕፃን 'እምቢ' ማለትን ከተማረች በኋላ አዋቂዎችን መታዘዝ የማያስፈልጋት ጊዜ መቼ እንደሆነ ለይታ እንድታውቅ የሚያስችሉ ሁኔታዎችን ሊያመቻቹላት ይችላሉ።




## ▶ እርዳታ ለመጠየቅ ልጅዎ ወዴት መሄድ እንደምትችል እንዴት መርዳት ይቻላል




ልጅዎ ወደ ማን ፊቷን ማዞር ትችላለች? ሁሉም ሕፃናት የችግሮቻቸው አጋር ሊሆኑ የሚችሉ ቢያንስ 3 ሰዎች ይኖሯቸዋል። እነዚህም እናታቸው ወይም አባታቸው፣ ታላቅ እህት ወይም ታላቅ ወንድም፣ አክስት፣ ጎረቤት፣ ወይም ሌላ ከቤተሰብ ውጪ የሆነ እርስዎና ልጅዎ ሊያምኑት የሚችሉት ሰው፣ ለምሳሌ የሌላ ልጅ እናት ሊሆኑ ይችላሉ።

ከእነዚህ ሰዎች አንዱ በማይኖርበት ጊዜ ወይም ትኩረት ካልሰጣቸው ሕፃናት ወደ ሌላው ሰው መሄድ እንደሚችሉ ሊያውቁት ያስፈልጋል። ሕፃኑን እርዳታ አጠያየቅ ያስተማሩት መሆኑንና ችግር ሲያጋጥመው እርዳታ ለመጠየቅ ወደ እነሱ ሊመጣ እንደሚችል ለሰዎቹም ይንገሩአቸው። የተለያዩ እርዳታዎችን ለመጠየቅ ሕፃኑ ወደ ሰዎች እንዴት መሄድ እንደሚችል ደጋግመው ያለማምዱት።

## ልጄ የወሲብ ጥቃት ደርሶባት እንደሆነ እንዴት ማወቅ እችላለሁ?

ጨቅላ ሕፃናት ጥቃቱ ሲደርስባቸው፣ ለመናገር ይፈሩ ይሆናል። አብዛኛውን ጊዜ ጥቃት ፈፃሚው ምንም እንዳይናገሩ ያስጠነቅቃቸዋል። አንዳንድ ጊዜ ሕፃኗ የሆነ ስህተት እንደፈፀመች ይሰማታል። ወይም ስለተደረገው ነገር እንዴት መነጋገር እንደምትችል ላታውቅ ትችላለች። ስለዚህ ሕፃናት ሁልጊዜ ስለ ጥቃት መናገር ስለማይፈልጉ፣ በልጅዎ ላይ ድርጊቱን ሊያሳዩ የሚችሉ ምልክቶችን ማየት ያስፈልግዎታል። የሚከተሉትን ምልክቶች ያስታውሉ:- እነዚህ ምልክቶች *ሁልጊዜ የጥቃት ውጤቶች ናቸው ባይባሉም፣* በተለይ ሕፃኗ አብዛኞቹን ምልክቶች የምታሳይ ከሆነ ሁኔታው ሁልጊዜ ሊያሳስብዎት የግድ ይላል።

*አንዳንድ በሰውነት ላይ የሚታዩ ምልክቶች:–*

- በሃፍረተ ስጋ ወይም በፊንጢጣ አካባቢ ሊገለፅ የማይችል የህመም ስሜት፣ እብጠት፣ መቅላት፣ ወይም የአፍ መድማት
- የተቀደደ ወይም ደም ያለበት ፓንት (የውስጥ ሱሪ)
- ከሕፃኗ ብልት፣ ወይም ፊንጢጣ ያልተለመደ ፈሳሽ ሲወጣ ወይም የአባላዘር በሽታ ምልክቶች ሲታዩ
- ሰገራ ወይም ሽንት መውጣት ሲያስቸግር፣ ወይም ከሽንት ጋር ወይም ከሰገራ ጋር ደም ተቀላቅሎ ሲወጣ
- ሰንበሮች፣ እራስ ምታት፣ ወይም እብጠት ያለው ማሳከክ

*ወሲባዊ ጥቃት የደረሰባቸው ሕፃናት ምናልባት:–*

- መታጠብ ያቆማሉ ወይም ከተለመደው በላይ በራሳቸው ይታጠባሉ፣ ወይም ልብሳቸውን ማውለቅ አይፈልጉም
- ወሲባዊ የሆኑ ጨዋታዎችን ከሌሎች ሕፃናት ጋር ወይም በመጨዋቻዎች አማካኝነት በደንብ እንደሚያውቁት ሆነው ይጫወታሉ፣ ወይም ብዙውን ጊዜ በእነሱ ዕድሜ ከሚጠበቀው በላይ ይጫወታሉ።
- በእነሱ ዕድሜ ከሚገኙ ሕፃናት በላይ ስለወሲባዊ ግንኙነት ያውቃሉ።

*የሀይልና የወሲባዊ ጥቃት ሰለባ የሆኑ ህፃናት ምናልባት:–*



- በጣም የሚፈሩ ይመስላሉ፣ ቁጡና ተጠራጣሪዎች፣ ወይም በድንገት የታወቁ ሰዎችንና ቦታዎችን ሲያዩ ይፈራሉ፣ ወይም ከወላጆቻቸው ጋር ብቻ መሆን ይፈልጋሉ
- ሚስጥረኛ ይሆናሉ ወይም አብዛኛውን ጊዜ ብቻቸውን መሆን ይፈልጋሉ
- ከእድሜአቸው በታች የበለጠ የሕፃንነት ባህርያትን ያሳያሉ
- የበለጠ ቁጡና ጠበኞች ይሆናሉ
- ከቤት ለመሸሽ ይሞክራሉ
- አብዛኛውን ጊዜ ሀዘን ይሰማቸዋል፣ ወይም ምንም ስሜት አይኖራቸውም
- መጥፎ ህልም ስለሚመጣባቸው የመተኛት ችግር አለባቸው፣ ጨለማን ይፈራሉ፣ በመኝታቸው ላይ ይሸናሉ
- መነካትን ወይም የሰውነት እንቅስቃሴዎችን ይፈራሉ

### ጥቃቱ መፈፀሙን የሚጠረጥሩ ከሆነ

ለመረጋጋት ይሞክሩ:: ልጅዎ የተፈፀመባትን ነገር ወይም የምታውቀውን ሁሉ እንድታሳይዎ ያባብሏት::

የበለጠ መረጃ ለማግኘት፣ ከልጅዎ ጋር የጨዋታ ሁኔታዎችን ያመቻቹ:: ህፃኑ በጨዋታዋ በኩል የሚያሳይዎትን ነገር በጥንቃቄ ይመልከቱ፣ ምክንያቱም ራሷን በደንብ ለመግለፅ የሚያስችላት በቂ ቃላት ወይም ምልክቶች ላይኖሯት ይችላሉ:: በድምፅዎና በአገላለፅዎ ልጅዎን እንደሚያምኑትና እንደማይቆጧት ያረጋግጡላት::

## ልጅዎ ወሲባዊ ጥቃት ተፈፅሞባት ከሆነ

ልጅዎ ወሲባዊ ጥቃት ተፈፅሞባት ከሆነ፣ እርስዎ ሊረዷት የሚችሉት:–

- የምታሳይዎትን ወይም የምትነግርዎትን ነገር የሚያምኑ ከሆነ ነው:: አንድ የሚያምኑት ወይም የሚያውቁት ሰው በልጅዎ ላይ እንደዚህ ዓይነቱን ድርጊት ይፈፅማል ብለው ለማመን ሊከብድዎት ይችላል፣ ነገር ግን ሕፃናት ስለወሲባዊ ጥቃት እምብዛም ፈጥረው አያወሩም:: አንዳንዶቹ ጥቃቱን ፈፃሚዎች ለወላጆች በጣም የሚቀርቡ ሰዎች ናቸው:: በዚህ ሁኔታ ሕፃናትን ለማቅረብ የተሻለ ዕድል ሲኖራቸው ወላጆችም ጉዳዩን ሪፖርት ከማድረግ እንዲታቀቡ ያደርጋቸዋል::
- ስለ ነገረችዎት ነገር ያመስግኗት፣ ምክንያቱም ሕፃናት ስለ ጥቃቱ መናገራቸው ትክክል መሆናቸውን እንዲያውቁ ይረዳቸዋልና ነው::
- የተለያዩ የመግባቢያ ዘዴዎችን በመጠቀም ጥቃቱ በሕፃኗ ስህተት ምክንያት ያለመሆኑንና እርስዎም እንደማይቆጧት በተቻለ መጠን ደግመው ደጋግመው ያረጋግጡላት::
- የልጅዎን ደህንነት ይጠብቁ:: ጥቃቱን የፈፀመው ሰውና ልጅዎ ለወደፊቱ መገናኘት እንዳይችሉ ያድርጉ:: ይህ የማይቻል ከሆነ ጥቃት ፈፃሚው በሚኖርበት ጊዜ እርስዎ ወይም ሌላ ስለተፈፀመው ጉዳይ የሚያውቅ ሰው ከልጅዎ ጋር መኖር እንዳለበት ያረጋግጡ::



- በአካልዋ ላይ የደረሰውን የጤና ችግር ያሳክሙ:: ምንም ዓይነት ምልክቶች ባይታይባትም እንኳ ልጅዎ የአባላዘር በሽታዎች እንድትመረመር ያድርጉ:: አንዳንድ የአባላዘር በሽታዎች ምንም ዓይነት ምልክቶች የላቸውም፣ ወይም ሕፃኗ ትልቅ እስከምትሆንበት ጊዜ ድረስ ምልክቶቹ አይታዩም::

እንደ ወላጅ እርስዎም እርዳታ ይፈልጋሉ:: ወላጆች ልጃቸው ወሲባዊ ጥቃት እንደደረሰባት ሲያውቁ የተለያዩ ስሜቶች (ለምሳሌ እምነት ማጣት፣ ንዴት፣ እና ሀዘን) ይፈራረቁባቸዋል:: በልጃቸው ላይ ስለተፈፀመው ድርጊት፣ ወላጆች እርስ በርሳቸው አንዱ ሌላውን ተጠያቂ ያደርጋሉ:: ስለ እነዚህ ስሜቶች ከአንድ ከሚያምኑት ሰው ጋር ቢነጋገሩበት ሊረዳዎት ይችላል:: በራስዎ በኩል ግን ትዕግስተኛ ይሁኑ:: እነዚህን ስሜቶች ለማስወገድ ረጅም ጊዜ ሊወስድብዎት ይችላል::

## በማህበረሰቡ ውስጥ ያሉትን ሕፃናት በሙሉ ደህንነት ለመጠበቅ

ስለ ወሲባዊ ጥቃት፣ የሕፃናት ደህንነት የተጠበቀ እንዳልሆነ ለመቀበል፣ ወይም በወሲባዊ ጥቃት ስለሚደርሱት ጉዳት ለመወያየት አብዛኞቹ ሰዎች ፈቃደኞች አይሆኑም። ነገር ግን ወሲባዊ ጥቃትን መከላከል የሚቻለው ሁሉም ሰው ስለ ጉዳዩ መነጋገር ሲችል ብቻ ነው።




የት/ቤቶች ፕሮግራሞችና ማህበራዊ ስብሰባዎች ማህበረሰቡን በሙሉ ስለ ወሲባዊ ጥቃት ማስተማር ይችላሉ። አጫጭር ጨዋታዎችን ማሳየትና ስለ ወሲባዊ ጥቃት የሚደረጉ ቀልዶች አንዳንድ ጊዜ በቀለለ ሁኔታ ሰዎች ስለ ጥቃቱ እንዲወያዩ ይረዳቸዋል።

ወሲባዊ ጥቃትን ለመከላከል ማህበረሰቡ በስፋት ሊሰራቸው የሚችሉ ስራዎች ከዚህ በታች ቀርበዋል።

- *ወርክሾፖች* – ለወላጆችና ለመምህራን – ወሲባዊ ጥቃትን ለመከላከል ከሕፃናት ጋር እንዴት መነጋገር እንደሚችሉ የሚረዳ። መወያየት የማይቻል ከሆነ የሚነበቡ የፅሑፍ ማቴሪያሎችን ለወላጆች ማቅረብ።
- *ስልጠና ለመምህራን*፣ በት/ቤት ለሚሰሩ ሠራተኞች፣ ለዶክተሮችና ለጤና ሰራተኞች – ይህም አንድ ሕፃን ጥቃቱ ደርሶበት ከሆነ ሊታዩ የሚችሉ ምልክቶችን ማጤን እንዲችሉና የጥቃቱ ሰለባ ከሆነችው ሕፃን ጋር እንዴት መወያየት እንደሚችሉ እንዲረዳቸው ስለ ሕፃናት ሥነ ምግባር ለመነጋገር ለት/ቤት ሠራተኞች ወርክሾፖችን ያካሂዱ።
- *ትምህርት* ለት/ቤት ተማሪዎች – ወሲባዊ ጥቃትን መከላከል እንዲችሉ ተማሪዎችን በጉዳዩ ዙሪያ ማስተማር ያስፈልጋል። ይህ ትምህርት ዕድሜአቸውን የሚመጥን ጤናማ የሆነ ወሲባዊ ትምህርትንም ሊያጠቃልል ይችላል።
- ጥቃቱ ሲፈፀም *ሪፖርት ማድረግ* – ለወደፊቱ እንዳይደገም ለመከላከል እንዲረዳ ሪፖርት ማድረግ ጠቃሚ ነው። የሕፃናትን ወሲባዊ ጥቃት እንዴት ሪፖርት ማድረግ እንደሚያስፈልግ የሚገልፁ መመሪያዎችን አፈላልጉ በማግኘት እነዚህ መረጃዎች ለወላጆች፣ ለመምህራን፣ ለጤና ሠራተኞችና ለሌሎችም በሕፃናት ላይ ስለሚደርስ ወሲባዊ ጥቃት ለማወቅ ለሚፈልጉ ሁሉ እንዲደርሳቸው ያድርጉ። ምንም ዓይነት መመሪያ ከሌለ መዘጋጀት እንዲችል ጥረት ያድርጉ።



ስለ ወሲባዊ ጥቃት ብዙ ሰዎች እያወቁ ሲመጡ፣ ድርጊቱ በሕፃናት ላይ እንዳይፈፀም በተሻለ ሁኔታ መከላከል እንችላለን